# ኢትዮጵያ፡ ለስኳር ልማት ሲባል አርብቶ አደሮች መሬታቸውን በግዳጅ እንዲለቁ ተደረገ

***መንግስት ከአካባቢው ተወላጅ ማህበረሰቦች ጋር ምክክር ማድረግ ፤እንዲሁም የካሣ ክፍያ መፈጸም አለበት***

(ናይሮቢ፣ ሰኔ 11 ቀን 2004 ዓ.ም.) በቂ ምክክር ሳያደርግ ወይም ተገቢውን የካሣ ክፍያ ሳይፈጽም በመንግስት የሚካሄድ የስኳር ልማትን ለማስፋፋት የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ነዋሪ የሆኑ አርብቶ አደሮችን በግዳጅ እያፈናቀለ ነው ሲል ሂዩማን ራይትስ ዎች ዛሬ ባወጣው ሪፖርት ገለጸ። ሪፖርቱ ከዚህ በፊት ያልታተሙ እና የመስኖ መስመሮችን፣ የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎችን እንዲሁም ሌሎች ለንግድ የሚውሉ ሰብሎችን ለማማረት የሚውል 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ሄክታር ጨምሮ በኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ የታቀደውን ሰፊ ልማት የሚያሳዩ የመንግስት ካርታዎችን ያካተተ ነው።

ሰማንያ አምስት ገጾች ያሉትና " 'ረሃብ ቢመጣ ምን ሊኮን ነው?': በኢትዮጵያ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ነዋሪዎች ላይ የተፈጸሙ በደሎች" በሚል ርዕስ የወጣው ይኸው ሪፖርት የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ሃይልና ማስፈራራትን በመጠቀም ነዋሪዎቹን ከጥንት ጀምሮ ከኖሩበት መሬት እንዴት እንዲለቁ እንደሚያደርጓቸውና ይህም የነዋሪዎቹን ሁለንተናዊ የኑሮ ሁኔታ ያለ ምንም የካሣ ክፍያና አማራጭ የኑሮ መሠረት በማስቀረት እንዴት አደጋ ላይ እንደጣለው የሚዘረዝር ነው። የመንግስት ባለስልጣናት በልማት ዕቅዱ ላይ ጥያቄ ባነሱ እና ተቃውሞአቸውን በገለጹ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች ላይ የዘፈቀደ እስር፣ድብደባና ሌሎች የሃይል እርምጃዎችን ወስደዋል።

"ኢትዮጵያ በኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ ያሰበችው ሰፊ የልማት ዕቅድ በዚያ የሚኖሩ ዜጎችን መብቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም ፣" ያሉት በሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ከፍተኛ ተመራማሪ ቤን ራውለንስ፣ "ልማት አቋራጭ መንገድ የለውም፤ በዚያ የሚገኘውን መሬት ለዘመናት የኑሮ መሠረታቸው አድርገው የኖሩ ሕዝቦች ሃሳባቸውን ሊጠየቁና ካሣ ሊከፈላቸው ይገባል።" ብለዋል።

እጅግ በጣም ሩቅ የሆነው እና ሰፊ የባሕል ስብጥር ከሚታይባቸው የምድራችን አካባቢዎች መካከል አንዱ የሆነው የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ቁጥራቸው 200,000 የሚደርስ በከፊል ግብርና እና ከብት ርቢ የሚተዳደሩና የራሳቸው መለያ ባሕሪያት ያሏቸው ስምንት ማህበረሰቦች የሚኖሩበት ሲሆን እነዚህ ሕዝቦች ዘመን መቆጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው የኖሩ ናቸው።የኑሮ ዘይቤአቸውና ማንነታቸው ከመሬት እና ለኦሞ ወንዝ ካላቸው ቅርበት ጋር የተቆራኘ ነው። የኦሞ ሸለቆ በኢትዮጵያ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ከኬንያ ድንበር አቅራቢያ የሚገኝ ሲሆን በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የማህበራዊና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስ ተብሎ እ.ኤ.አ በ1980 ተሰይሟል።

በኦሞ ሸለቆ ለማምጣት የታቀደው ከፍተኛ ለውጥ በኦሞ ወንዝ ላይ ከሚገነባውና በከፍታው በአፍሪካ ተወዳዳሪ ከሌለው አወዛጋቢው የጊቤ ሦስት የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ጋር የተያያዘ ነው። በወንዙ የታችኛው ክፍል የሚካሄደው የስኳር ልማት በመስኖ የሚለማ ነው። በጊቤ ግድብ ፕሮጀክት ላይ የተካሄዱ አንዳንድ ነፃ ግምገማዎች ያሉ ቢሆንም በኦሞ ሸለቆ የሚካሄደው የስኳር ልማት እና ሌሎች ለንግድ የሚውሉ ሰብሎች ግብርና እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን አካባቢያዊና ባሕላዊ ተጽዕኖ አስመልክቶ የተካሄደ አንድም ግምገማ የኢትዮጵያ መንግስት እስከዛሬ ይፋ አላደረገም።

ሂዩማን ራይትስ ዎች በሰኔ 2003 ዓ.ም. ከ 35 በላይ የአካባቢው ነዋሪዎችና ከ 10 የእርዳታ ሰጪ ሀገራት ተወካዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ያደረገ ሲሆን ከዚያ ጊዜ በኋላም ቢያንስ 30 ሌሎች እማኞችን አነጋግሮአል። ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት ነዋሪዎችን ለማስፈራራትና ከስኳር ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ለማፈን የጦር ሠራዊት አባላት በመንደሮቹ በየጊዜው ቅኝት ያደርጉ ነበር። ወታደሮቹም (የመንደርተኞቹን) ከብቶች ይሰርቃሉ ወይም ይገድላሉ።

"ምን ልበላ ነው?" ይላሉ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል የሆኑ አንድ ሰው ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሲናገሩ። "ከብቶቼን በሙሉ ወስጄ እንድሸጥና አንድ ብቻ ከቤቴ እንዳስቀር ነገሩኝ። አንዱን ከብት ምን ላደርገው ነው? እኔ ሙርሲ ነኝ። ረሃብ ቢመጣ የላም አንገት ወግቼ ደም እጠጣለሁ። ከብቶቼን ሁሉ ለገንዘብ ከሸጥናቸው እንዴት ነው የምንበላው?"

ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ በኋላ ያሰባሰባቸው ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የክልሉ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ሃይሎች ባላፈው ዓመት የስኳር ልማቱን ለማካሄድ በሚከለለው ቦታ እያረሱ ይኖሩ ከነበሩ የአካባቢው ተወላጆች መሬት በሃይል ነጥቀው ወስደዋል። ነዋሪዎች በሃይል መፈናቀላቸውን እና የመሬት ምንጣሮ መካሄዱን የሚያመላክቱ ሪፖርቶችም እየበረከቱ መጥተዋል።

የኦሞ ወንዝን ውሃ ማግኘት በሸለቆው ውስጥ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮች የምግብ ዋስትና እና የኑሮ ዘይቤ እጅግ አስፈላጊ ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የከብቶቻቸውን ቁጥር መቀነስ እና በአንድ አካባቢ መስፈር እንዳለባቸው እንዲሁም በኦሞ ወንዝ ያላቸው ተጠቃሚነትም እንደሚቀር የክልሉ ባለስልጣናት ያለምንም ተጨማሪ ውይይት ገልጸውላቸዋል።

ከሰኔ ወር 2004 ጀምሮ የመስኖ መስመሮች ቁፋሮና የመሬት ምንጠራ የተካሄደ ሲሆን በወንዙ ምስራቃዊ ዳርቻም ስኳር ማምረት ተጀምሯል። በሂዩማን ራይትስ ዎች የተነሱ የመንግስት ካርታዎች ፎቶግራፎች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ወቅት የስኳር ልማት እየተካሄደ ያለው “የስኳር ብሎክ አንድ” ተብሎ ከተሰየመው ክልል የተወሰነ ክፍል ላይ ሲሆን ለስኳር ልማት ተብለው የሚወሰዱ ሁለት ተጨማሪ ብሎኮችም በቀጣይነት ይጨመራሉ። በአሁኑ ወቅት ያለው የኢትዮጵያ የጊቤ ግድብ የተጽዕኖ ግምገማ የስኳር ልማቱ እና የመስኖ ሥራው በኦሞ ወንዝ ፍሰት ላይ ወይም ከወንዙ ግርጌ በሚገኘው የቱርካና ሐይቅ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጸዕኖ ያካተተ አይደለም።ካርታዎቹ የሚያሳዩት ግዙፍ የመስኖ መስመሮች ዝርጋታ ከዚህ ቀደም የተካሄደው ግምገማ በቂ እንዳልነበር የሚጠቁም ነው።

ዕቅዱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ በኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ቢያንስ 200,000 ሰዎችን እንዲሁም ድንበር ተሻግሮ በሚገኘውና 90 በመቶ የሚደርሰውን ውሃውን ከኦሞ ወንዝ በሚያገኘው በቱርካና ሐይቅ አካባቢ የሚኖሩ ሌሎች 300,000 ኬንያውያንን ሕይወት የሚነካ ነው። የጊቤ ሦስት ግድብ እና በመስኖ የሚካሄደው የንግድ ግብርና የሚያስከትሉትን ጥምር ተጽዕኖ የሚፈትሽ አዲስ የአካባቢ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድ ኬንያ ግፊት ማድረግ አለባት ብሏል ሂዩማን ራይትስ ዎች።

እነዚህ የኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ነዋሪዎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህሕላዊ መብቶች የሚጋፋ ድርጊቶች፣ ትርጉም ያለው ምክክር፣የነዋሪዎቹ ስምምነት እንዲሁም ለሚወሰደው መሬት፣ለሚጠፋው የኑሮ መሠረት እና የምግብ ዋስትና የካሣ ክፍያ እንዲፈጸም፤ በተለይም ተወላጅ ነዋሪዎችን ከታሪካዊ መኖሪያቸው ማፈናቀል ፍጹም የመጨረሻ አማራጭ ብቻ ተደርጎ መወሰድ አለበት በማለት የሚደነግጉትን ብሔራዊና ዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆች በመጣስ የሚፈጸሙ ናቸው።

የተወላጅ ሕዝቦች መብቶች በኢትዮጵያ ሕጎችና በሕገ መንግስቱ፣በተባባሩት መንግስታት ድርጅት የተወላጅ ሕዝቦች መብቶች ድንጋጌ እና በአፍሪካ የሰብአዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን ትርጓሜ በተሰጠው እንደ የአፍሪካ የሰብአዊ እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር ባሉ አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ተቋማት ዕውቅና ያገኙ መብቶች ናቸው። እነዚህ ሕጎች እና ስምምነቶች ተወላጅ ሕዝቦች በመሬታቸው ላይ ላላቸው የንብረት ባለቤትነት መብት  መንግስት ዕውቅና የመስጠት ግዴታ እንዳለበትና ከመኖሪያቸው ሊፈናቀሉ የሚችሉትም ያለ ተጽዕኖ ስምምነታቸው በቅድሚያ ተጠይቆ ሲስማሙ ብቻ መሆን እንዳለበት ይደነግጋሉ። ስምምነታቸው ከተገኘ በኋላም ቢሆን ለሚያጡት መሬት፣ንብረት እና የኑሮ መሠረት ሙሉ የካሣ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች እንዳረጋገጠው ኢትዮጵያ ተወላጅ ነዋሪዎቹ በመሬታቸው ላይ ያላቸውን የይዞታ ዋስትና ጨምሮ ለየትኛውም መብታቸው ዕውቅና አልሰጠችም። የኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎችን ስምምነት ማግኘት ይቅርና በተለይ የአብዛኞቹን የአካባቢው ነዋሪዎች እጅግ አናሳ የመደበኛ ትምህርት ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከነዋሪዎቹ ጋር በቂ ምክክር እንኳ አላደረገችም።

ሂዩማን ራይትስ ዎች በጉዳዩ ላይ ላነሳቸው ስጋቶች የኢትዮጵያ መንግስት በአካባቢው የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ለተወላጅ ነዋሪዎች  የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ የሚያስገኘውን ጥቅም በመጥቀስ ምላሽ ሰጥቷል።በልማቱ ለሚነኩት ማህበረሰቦች የሥራ ዕድል ማግኘት እሰየው የሚባል ጥቅም ሊሆን ይችላል። ይሁንና ወደፊት የሚገኝ የሥራ እድል መኖሩ፣ በእርሻ ልማቱ እንቅስቃሴ ላይ ጥልቅ ጥናት እስኪደረግ፣ተወላጅ ነዋሪዎቹ በመሬታቸው ላይ ያሏቸው መብቶች እስኪረጋገጡ፣ ስምምነታቸው እስኪገኝና እና ነዋሪዎቹን አፈናቅሎ መሬታቸውን የመውሰዱ ተግባር እጅግ አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ መሆኑ ተረጋግጦ  ካሣ እስኪከፈላቸው ድረስ መንግስት በአካባቢው የሚያካሂደውን የእርሻ ልማት እንቅስቃሴ በአስቸኳይ ማቆም ያለበት መሆኑን አያስቀረውም ብሏል ሂዩማን ራይትስ ዎች።

በርካታ ዓለማቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጊቤ ሦስት የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሊያስከትል የሚችለውን ማህበራዊ እና የአካባቢ ተጽዕኖ በማንሳት ስጋታቸውን የገለጹ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት በጉዳዩ ላይ ባሳየው ግልጽነት የጎደለው አካሄድና ነፃ የሆነ ግምገማ ባለማድረጉ ወቀሳቸውን ሰንዝረዋል።ምክንያቱን በይፋ ባይገልጽም የኢትዮጵያ መንግስት የዓለም ባንክ እና የአፍሪካ ልማት ባንክ የጊቤ ግድብ ፕሮጀክትን በገንዘብ እንዲደግፉ አቅርቦ የነበረውን ጥያቄ አንስቷል።የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴም ፕሮጀክቱ በቱርካና ሐይቅ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክቶ ተጨማሪ ነፃ የሆነ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ ፕሮጀክቱ እንዲቆም ሀሳብ አቅርቧል።

የኢትዮጵያ መንግስት የበጀቱን ከፍተኛ ድርሻ የሚያሟላው ከዓለማቀፍ ለጋሾች በሚያገኘው ዕርዳታ ነው። የጸጥታ ሃይሎች እና የክልልና የወረዳ አስተዳደር ባለስልጣናትም ምንም ምክክር ሳይደረግና ለመብታቸው ዕውቅና ባልተሰጠበት ሁኔታ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን ለቀው መሄድ እንዳለባቸው በመንገር የስኳር ልማት ዕቅዱን እያስፈጸሙ ናቸው። የመሠረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ (ፒቢኤስ) በመባል የሚታወቀውና በበርካታ ለጋሾች የገንዘብ ድጋፍ የሚካሄደው ፕሮግራም ለጤና፣ ለትምህርት እና ለሌሎች ዘርፎች የሚውል በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር የሚገኝበት ሲሆን የደቡብ ብሔሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልልን ጨምሮ

በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ የወረዳ አስተዳደር ባለስልጣናት ደመወዝም ከዚሁ ፕሮግራም በሚገኝ ገንዘብ የሚከፈል ነው። ለፒቢኤስ ፕሮግራም ትልቁን የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉትም ብሪታንያ፣የአውሮፓ ህብረት፣ኔዘርላንድስ እና ጀርመን ናቸው።

የልማት እንቅስቃሴዎቹ ከሀገሪቱ ሕጎችና ከዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ መካሄድ እስኪችሉ ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት የጊቤ ሦስትን ግንባታ እና ተያይዞ የሚካሄደውን የስኳር ልማት እርሻ እንዲያቆም ሂዩማን ራይትስ ዎች ጥሪውን አቅርቧል። በደቡብ ኦሞ ተጨማሪ ኢንዱስትሪያዊ የልማት ሥራ ከማካሄዱ በፊት የኢትዮጵያ መንግስት የኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ማህበረሰቦች ለዘመናት በኖሩበት መሬታቸው ላይ ያሏቸውን መብቶች ማክበር፣መሬታቸው ለምን አገልግሎት ሊውል እንደታሰበ እና የካሣ ክፍያን አስመልክቶ ትርጉም ያለው ውይይት ከነዋሪዎቹ ጋር ማድረግ አለበት። ለጋሾችም የሚሰጡት ገንዘብ በግዳጅ ለማፈናቀል ወይም የተወላጅ ማህበረሰቦችን መሬት በሕገ ወጥ መንገድ ለመውረስ እየዋለ እንዳልሆነ ማረጋገጥ አለባቸው ብሏል ሂዩማን ራይትስ ዎች።

"ኢትዮጵያ የተፋጠነ የኢኮኖሚ ልማትን ለማምጣት ያላት ፍላጎት የሚደገፍ ነው፤ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኦሞ ሸለቆ እየታየ ያለው ሁኔታ በአካባቢው ተወላጅ ማህበረሰቦች መብቶች እና በኑሮ መሠረታቸው ላይ ተቀባይነት የሌለው ጫና እያሳደረ ነው፣" ያሉት ራውለንስ "መንግስት ተፈላጊዎቹን መመዘኛዎች እስኪያሟላ ድረስ ሂደቱን ማቆም አለበት፤ለጋሾችም የሚሰጡት ዕርዳታ የሚፈጸሙትን በደሎች እያገዘ እንዳልሆነ ማረጋገጥ አለባቸው።" በማለት አክለዋል።

**ከ "ረሃብ ቢመጣ ምን ይኮናል" የተወሰዱ ጥቅሶች**

በስኳር [ልማት] ላይ ከመንግስት ጋር የማይስማሙ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን መንግስት በሃይል አስገድዶ በሌላ ቦታ ሊያሰፍራቸው እንደሚችል በመፍራት ብዙም አይናገሩም። እዚህ መንግስትን በጣም ነው የምንፈራው። ስጋትህን ከገለጽህ፣ እስር ቤት መግባትህ ነው።" --የቦዲ ብሔረሰብ አባል፣ ሰኔ 2003

"ወቅቱ ደረቅ በሚሆንበት ጊዜ ችግር ይፈጠራል። አሁን ውሃ አለ፣ነገር ግን ውሃ በማይኖርበት ወቅት ወደ ኦሞ ወንዝ የማንመለስ ከሆነ መንግስት ውሃ እንዲያቀርብልን እንፈልጋለን፤ የማያቀርብልን ከሆነ ግን እኛም ከብቶቻችንም እንሞታለን። ሆነም ቀረ ግን ወደ ኦሞ ወንዝ እንሄዳለን፤ እለዚያ እንሞታለን፣ከፈለጉ እዚያ ሊገድሉን ይችላሉ።" --የሙርሲ መንደር ነዋሪ፣ ሰኔ 2003

"ምን ልበላ ነው? ከብቶቼን በሙሉ ወስጄ እንድሸጥና አንድ ብቻ ከቤቴ እንዳስቀር ነገሩኝ። አንዱን ከብት ምን ላደርገው ነው? እኔ ሙርሲ ነኝ። ረሃብ ቢመጣ የላም አንገት ወግቼ ደም እጠጣለሁ። ከብቶቼን ሁሉ ለገንዘብ ከሸጥናቸው እንዴት ነው የምንበላው? ጋብቻ ስንፈጽም የምንሰጠው ከብት ነው። በምን እንጋባ? ምን እንብላ? ረሃብ ሲመጣ ልጆቻችንን ምን ልናበላቸው ነው? ዶሮ ብቻ ብናረባ መረቃቸውን እንጠጣለን ወይስ እናልባቸዋለን...? 'ይህ የኔ መሬት ነው [እናንተ] እንደ ዝንጀሮ ወደ ጫካ ሂዱ።'ይላሉ ደገኞቹ ኢትዮጵያውያን።"
-የሙርሲ ብሄረሰብ አባል የከብቶችን አስፈላጊነት ሲያብራሩ፣ ታህሳስ 2003

"የመንግስት ባለስልጣናት የክዌጉ እና የቦዲ ብሔረሰብ አባላትን ማሳ መነጠሩ። ሰፊ ቦታ መንጥረው ማሽላቸውን ነቃቀሉባቸው። ማሽላው እየደረሰ ነበር፤ተሽከርካሪ አምጥተው ማሳውን ከገለበጡ በኋላ ማሽላውን ወረወሩት። የክዌጉዎቹ ማሳዎች ተገለብጠዋል። አንዳንድ ክዌጉዎች አሁን ምንም የላቸውም። ማሽላቸው ከተገለበጠ ምን ሊበሉ ነው? ለልጆቻቸውስ ምን ይሰጧቸዋል?" -አንድ ሰው በቦዲ እና በክዌጉ ብሔረሰብ አባላት የእርሻ መሬቶች ላይ በታህሳስ 2004 የተፈጸመውን ሲገልጹ

"ከብቶቹ በሙሉ ለመንግስት ከተሰጡ በአካባቢዎቹ ትልቅ ችግር ይፈጠራል። ድርቅ የአፍሪካን ቀንድ አካባቢ እንዲህ ክፉኛ በመታበት በአሁኑ ወቅት እነዚህ ሰዎች ምን ይበላሉ? አሁን ግድቡ ተገንብቷል፣ወንዙ ምንም ውሃ የለውም፣መሬቱ ተወስዷል፣ከብቱ ለመንግስት ተሰጥቶ እነዚህ ምስኪን ሰዎች በችጋር ጊዜ ምን ይሆናሉ? ከብት አርቢዎችን ለማጥፋት የሚፈልጉት ሰዎች በቀን ሦስት ጊዜ የሚበሉ ናቸው። ረሃብ ቢመጣ ምን ይኮናል?" --የሙርሲ ብሔረሰብ አባል ግንቦት 2003